CARD
Center for Advancement of Rights and Democracy

# የፀረ-ጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃዎች መመሪያ




በመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል የተዘጋጀ

# ማውጫ

3 የሐሰት ዜና

4 ሁለቱ ሀሳቦች, መረጃን ማሳሳት እና መረጃን ማዛባት

5 የሐሰት ዜናን እንዴት መለየት እንችላለን

6 እውነታን ማረጋገጥ

8 እውነታን የማረጋገጫ ዘዴዎች ወይም ስልቶች

9 ኮቪድ 19 እና የሐሰት ዜና

10 የማህበራዊ ሚድያ እርመጃዎች

11 የጥላቻ ንግግር

13 የጥላቻ ንግግርን እንዴት እንከላከል

# ሐሰተኛ ዜና ምንድነው?

**ሐሰተኛ ዜና ሲባል የዜና ወይም የመረጃ ዓይነት ሲሆን ይዘቱም ሆነ ብሎ መረጃን ማዛባት ወይንም የፈጠራ ወሬን በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን እና ኦን ላይን ሚድያዎች ላይ መንዛት ነው። በተለይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ይዘወተራል።**




**አብዛኛው የሐሰት ዜና ሁለት ሃሳቦችን ደባልቆ ይይዛል እነሱም፡ መረጃ ማሳሳት እና መረጃ ማዛባት ናቸው።**

# ሁለቱ ሀሳቦች

## መረጃን ማሳሳት እና መረጃን ማዛባት

### መረጃ መበከል

ማለት እውነት የሆነ መረጃ ላይ ተመስርቶ አንድን ሰው ወይም ድርጅት ወይም ሀገር ላይ **ጉዳት ለማድረስ በማቀድ** የተዛባ መረጃን መፍጠር ነው።

### መረጃ ማሳሳት

ማለት በስህተት የተሰራጨ ሐሰተኛ መረጃ ማለት ሲሆን ነገር ግን **ያሰራጨው ሰው እውነት ነው ብሎ ያምናል።**

### መረጃ ማዛባት

ማለት ሀሰተኛ እንደሆነ እየታወቀ የሚደረግ የሀሰተኛ መረጃ ማሰራጨት ነው። ይህ ዓይነቱ መረጃ **የታሰበና የታቀደ ውሸት** ሲሆን ይህም መረጃ እኩይ አላማ ባነገቡ ሰዎች የሚደረግ የሀሰተኛ መረጃ ማሰረጨት ነው።




ምንጭ: firstdraftnews.org

# ሐሰተኛ ዜናን እንዴት መለየት እንችላለን?

## በማን ተጻፈ?

አብዛኛው የሐሰት መልዕክቶች(በተለይም ከሌላ ሰው የሚተላለፉ) በማን እንደተጻፉ አይገልጹም። በማን እንደተጻፉ ካላወቅን፤እንዴት ማመን እንችላለን?

**መልዕክቱ በማን እነደተጻፈ ካላረጋገጡ እና ከየት እንደመጣ ካላወቁ - ይጠንቀቁ!**

## የተባለውን ነገር ማረጋገጥ ይችላሉ?

አብዛኛው የሐሰት መልዕክቶች ምንጭ አይገልጹም ወይም ከገለጹ የማያስተማምኑ ምንጮችን የፈጠራ የዜና ማሰራጫዎችን ይጠቀማሉ። አንዳንድ የሐሰት ዜና አሰራጪዎች እውነታኛ እንደሆኑ ይናገራሉ ነገር ግን ይህንንም የሚሉት ውሸታቸውን ነው።

**ስለተባለው ነገር እርግጠኛ ካልሆኑ እና በአስተማማኝ ምንጭ ካልተደገፉ ይጠንቀቁ!**

whois.com/whois ይህን ድህረ ገጽ ማን ከበስተጀርባ እንዳለ ለማወቅ ይረዳናል።

## መረጃው ምን አይነት ስሜት እንዲሰማችሁ ያደርጋል?

ቀጥታ መስመር(online) ላይ የሚለጠፉ አብዛኛው ጉዳዮች የሚያስቆጡ ወይም ስሜትን የሚነኩ ርዕሶች ሲሆኑ፤ ሀይማኖትን፣ ጎሳ ወይም ነገድን ወይንም የሃይማኖት እና የጎሳ ቦታዎች ላይ ጥቃት እንዲኖር ማነሳሳትን ወዘተ... እና ምስሎችን፣ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን እና ድምጾችንም ያጠቃልላል።

**መረጃው የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ እንዲሁም የሚያስደነግጥ ምስል ወይም ተንቀሳቃሽ ምስሎችን የያዘ ከሆነ - ይጠንቀቁ!**

መረጃውን ከማሰራጨትዎ በፊት፡ የተስተካከለ ወይም ከዚህ ቀደም በሌላ ሁኔታና ቦታ የተፈጠረው ተስተካክሎ እንዳይሆን ያረጋግጡ።

እነዚህን የጠቀሙ TinEye, Exif data viewer, Google reverse image search

## የፈጠራ አለመሆኑ እርግጠኛ ኖት(ነዎት)?

እርግጠኛና አስተማማኝ እንዲሁም ተቀራራቢ መረጃ በአግባቡ እና በሰዓቱ ለማግኘት ኢትዮጵያ ወስጥ ቢከብድም አንድን መረጃ 100% እርግጠኛ ካልሆኑ ለሌሎች አያጋሩ።

**አሁንም እርግጠኛ ያለሆኑበትን መልዕክት ለሌላው አያጋሩ - ይጠንቀቁ!**

*ምንጭ: africacheck.org*

# እውነታን ማረጋገጥ

**አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር እውነታ ከሚረጋገጥበት ዋነኛ መንገድ እውነታው ሳይታወቅ ከመሰራጨቱ በፊት መሆን የነበረበት ቢሆንም አሁን ግን ህዝቡጋ ከደረሰ በኋላ ነው። እንደነዚህ አይነት የ“ex-post” እውነታ ማረጋገጫዎች ፖለቲከኞችን እና ሌሎች ታዋቂ ሰዎች ለሚሰጧቸው መግለጫዎች እውነተኛነት እና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚጥር ነው።**

**ለህዝቡ መረጃ በሚወጣበት ጊዜ በእውነታ ማረጋገጥ እና ማጣራት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ቀዳሚና የታወቀውን ምንጭ በማየት የተባለውን ያጸናሉ(ያረጋግጣሉ) ወይም ይቃወማሉ።**




**አስፈላጊውን እና ትክክለኛውን ውጤት ለማግኘት የአንድን መረጃ ዋናውን ወይም ትክክለኛ ምስሉን በመለየትና ያጋሩትን መረጃ ትክክለኛ ይዘት እና ምንጭ ማጣራት እራሳችንን እውነታውን በማረጋገጥ እና በማጣራት ሁኔታ ውስጥ ልናገኝ እንችላለን።**

## የምንጮችን አሳማኝነት ለማረጋገጥ የሚረዱ መንገዶች

- አስፈላጊ ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የማረጋገጫ መሳሪያዎችን መጠቀም

## የማስጠንቀቂያ ምልክት”ን በቀላል ዘዴ የማረጋገጥ መንገድ

- ይዘቱ የመጀመሪያና ዋና ነው፤ ወይስ ከዚህ በፊት የወጡ ዘገባዎችን ሞራርዶና አስተካክሎ በሚያሳስት መልኩ የተቀመጠ ነው?
- በዲጂታል መንገድ ይዘቱ ተጽኖ ተፈጥሮበታል?
- በይዘቱ ላይ የሚታዩ ምንጮችን በመጠቀም የምስል እና የተንሳቃሽ ምስልን ቦታና ሰዐት ማረጋገጥ ይቻላል?

# የማስጠንቀቂያ ምልክትን በተገቢ ሁኔታ ለማግኘት፤ መጀመሪያ የተለመዱትን አሳሳች ምስሎችና የሐሰት ይዘቶች መለየት ይኖረብናል።

## የተሳሳተ ቦታ/የተሳሳተ ጊዜ(Wrong place/ Wrong time)

አሁን በኢትዮጵያ ባለው ነባራዊ የቆየ ምስልን ከሚገልጸው ሃሳብ ውጪ በአዲስ ሃሳብ በመቀየር እንደ አዲስ ማጋራት የተለመደው ይዘትን የማሳሳት መንገድ ነው። በአብዛኛው ሳይታሰብ በሚደረግ ማጋራት የሚከሰተው ስርጭት ወደ ኋላ ተመልሶ ለማስተካከል የሚከብድ ይሆናል።

## የተዛባ ይዘት(Manipulated Content)

የምስል ወይም የተንቀሳቃሽ ምስል ማዛቢያ ሶፍት ዌር በመጠቀም አንድን ይዘት ዲጂታል በሆነ መንገድ ማስተካከል ወይም መቀየር ማለት ነው።
ለአብነት ያክል በቅርቡ በየዩኒቨርሲቲዎች የተከሰቱትን ውጥረት እና ግጭቶችን በተመለከተ የተለቀቁትን ምስሎች መመልከት የቻላል።

## የታቀደ ይዘት (Staged Content)

ታስቦና ታቅዶ ለማሳሳት የተፈጠረ ወይም የተጋራ ይዘት ነው።




ምንጭ UNESCO

# እውነታን የማረጋገጫ ዘዴዎች ወይም ስልቶች

## ሪቨርስ ኢሜጅ(REVERSE IMAGE)

ምስሎችን የፍለጋ አውታር ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ የምስል ፋይሎችን ወስዶ በማስገባት የተመሳሳይ ምስሎችን ውጤት ያሳያል።

Google Reverse Image Search, TinEye, ወይም RevEye, ከነዚህ አንዱን በመጠቀም አንድን ምስል ለሌላ ሁኔታ ወይም ጥያቄ እንደገና (Recycled) መጠቀምና አለመጠቀሙን ማጣራት ይቻላል።

**ሪቨርስ ኢሜጅ የፍለጋ አውታር አንድን የቆየ ምስል በውስጡ ከያዘው አንድና በብዙህሺ የሚቆጠሩ ምስሎች ያሉበት የምስል ዳታ ቤዝ (data base) ውስጥ በማውጣት ያሳያል።**

## የቱብ ዳታ ቪወር(YOUTUBE DATA VIEWER)

የአንድን ተንቀሳቃሽ ምስል የቀድሞ ሁኔታ ወይም አፕሎድ ለማየት የሚያስችል “የተንቀሳቃሽ ምስል መፈለጊያ አውታር(Reverse video serach)” ለሁሉም ሰው አገልግሎት የሚውል ባይኖርም እንደ Amnesty’s YouTube Data Viewer, InVID እና NewsCheck ያሉትን ተምብኔይልስ በመጠቀም የዩቱብ ተንቀሳቃሽ የቀድሞ ምስሎችን መጫናቸውን ሊያሳይ ይችላል።

**እነዚህ ስልቶች/ዘዴዎች ምስሉ የተጫነበትን ትክክለኛ ሰዐት ያሳያሉ**

## ኤግዚፍ ቪወር(EXIF VIEWER)

ይህ አይነቱ ስልት ብዙ ዳታዎችን በተንቀሳቃሽ ስልክ እና ዲጂታል ካሜራ እዛው ሁኔታው ሲከሰት የተነሱና የተፈጠሩ ምስሎችን ከምስል ይዘት ጋር ተያይዞየሚገኝ ሜታ ዳታ ነው። እነዚህም በውስጣቸው ትክክለኛ ሰዐትና ቦታ፣ የቦታ ሜታ ዳታ፣ የዲቫይስ ዳታ እና የብርሃን መቼት መረጃ ይይዛሉ።

**የኤግዚፍ ዳታ ዋነኛ ችግር/ገደብ የምስል ይዘቶቹ በማህበራዊ ሚድያ ይገደባሉ፣ ከነዚህም ትዊተር ወይም ፌስቡክ ላይ የተጋሩ ምስሎች ኤግዚፍ ዳታን አያሳዩም። የሚሰተካከሉ/የሚለወጡ ስለሆኑ ተጨማሪ ማረጋገጫ ይጠይቃሉ።**



# ኮቪድ 19 እና
# የሐሰት ዜና

የኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ 19) በሽታ መንስኤ አዲስ ግኝት የሆነው የኮሮና ቫይረስ ዝርያ ነው።ይህም አዲስ የቫይረስ አይነት ሲሆን ከሳርስ(SARS) እና ከአንዳንድ የጉንፋን ቫይረሶች ጋር ተመሳሳይ የዘር(የቤተሰብ) አይነትን ይጋራል። ኮቪድ የሚለው የምስጻረ ቃል ስያሜ የሚወክለው፡ - “ኮ” ኮሮና የሚለውን ለመወከል ሲሆን፣ “ቪ” ቫይረስ የሚለውን ሲወክል፣ ድ(ዲ) ዲዘስ ወይም በሽታ የሚለውን ያመለክታል። ከዚህ ስያሜ በፊት 2019 ኤን ኮቭ(2019nCov) ወይም 2019 ኖቭል ኮሮና ቫይረስ ተብሎ ይጠራ ነበር።

በዚህ በሽታ የተያዙ ሰዎች አነስተኛ ወይም መካከለኛ የሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም የሰማቸዋል ይህም ያለምንም የተለየ የህክምና እርዳታ ማገገም ይችላሉ። እድሜያቸው የገፋ ሰዎች እናተጓዳኝ በሽታ ያለባቸው ሰዎች በጠና ሊታመሙ ይችላሉ፣ ከነዚህም መካከል የስኳር በሽታ፣ የልብና የደም ባንባ በሽታ፣ ከባድ የመተንፈሻ አካል በሽታ እንዲሁም የካንሰር በሽታ ያለባቸው ይገኙበታል።







ስለ በሽታው ከመጠን ያለፈ የተሳሳተ መረጃ ስርጭት በሽታውን በአግባቡ መከላከል እንዳይቻል በአለም አቀፍ ደረጃከባድ አድርጎታል። የአለም የጤና ድርጅት ስለዚህ “ከመጠን ያለፈ የተሳሳተ መረጃ ስርጭት” ሲያብራራ “ከመጠን ያለፈ የመረጃ ጥቂቱ ትክክል እና ጥቂቱ ትክክል ያልሆነ መረጃ መኖሩ ሰዎች ትክክለኛውን ምንጭ ለማወቅ እና ተአማኒነት ያለውን መመሪያ ለመከተል በአስፈለጋቸው ሰዐት ለማግኘት ይቸገራሉ።”

*ምንጭ: የአለም ጤና ድርጅት WHO &France24*

# የማህበራዊ ሚድያ እርመጃዎች

ጎግል እንዳሳወቀው 24 ሰዐት የሚሰሩ ያጋጠሙ-ሀተታዎችን (a 24-hour incident-response team) የሚያዩ ቡድኖች በማዘጋጀት ማንኛውንም አይነት የተሳሳተ መረጃ ከፍለጋ አውታር ላይ እና ዩቱብ ላይ እነዲሁም ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን መረጃ ከአለም ጤና ድርጅት ድረ ገጽ ስለኮሮና በሽታ መረጃ ያቀርባል።

ዩቱብ የተለያዩ ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ከፕላት ፎረሙ ላይ ያነሳ ሲሆን ፌስቡክም የተለጠፉ (ፖስቶችን) ከፕላት ፎረሙ ከኢንስታግራም ጨምሮ ለታዘዙ መድሃኒቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በሚለጠፉበት ጊዜ ከፕላት ፎረሙ ላይ እስወግዷል።

ፌስቡክ ሃገራት ስለኮሮና ቫይረስ ተገቢውን መረጃ እንዲያገኙ የመረጃ ማዕከላትን አዘጋጅቷል

**ኢትዮጵያ ውስጥ የተረጋገጡ የኮሮና ቫይረስ በሽታ መረጃዎችን የምናገኝባቸው ሳይቶች የሚከተሉት ናቸው፡**

- Ministry of Health - Ethiopia Website
- Lia Tadesse Facebook Page
- Ethiopian Public Health Institute Facebook page
- UNICEF - Ethiopia
- World Health Organization African Region
- Africa CDC
- World Health Organization Ethiopia
- UNICEF

ምንጭ: France24

# የጥላቻ ንግግር




የጥላቻ ንግግር ማለት በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ላይ ያነጣጠረ፣ ዘርን፣ ብሄርን፣ ፆታንና የመሳሰሉትን መሰረት በማድረግ ጥላቻን፣ መድሎን፣ ወይም ጥቃትን የሚያበረታታ ገለፃ ማለት ነው። የጥላቻ ንግግር አደገኝነት በብዙ የአለማችን ክፍል የታወቀ ሲሆን አሳዛኝ ክስተቶችንም ያስከተለ ነው።




የጥላቻ ንግግር ፒራሚድ

*ምንጭ: Article 19*

# ከማጋራትዎ በፊት ይህንን ያጣሩ/ያስተውሉ

## የተናጋሪው/ዋ ሁኔታ

- ተናጋሪው/ዋ ያሉበት ሁኔታ ምን ያህል ንግግሩ ላይ ተፅዕኖ አለው?
- የሚደመጥ/የምትደመጥ ሰዎች ናቸው ወይስ ችላ የሚባሉ?

## የንግግሩ ተደራሽነት

- ንግግሩ ምን ያህል የመዳረስ አቅም አለው?
- የባህሪ ንድፍ ይታይበታል?

## የንግግሩ ግቦች

- ንግግሩ ተናጋሪዎቹንና ፍላጎታቸውን እንዴት ይጠቅማል?
- ንግግሩ ጉዳት ለማድረስ ያለመ ነው?

## የንግግሩ ይዘት

- ንግግሩ አደገኛ ነው?
- በሌሎች ላይ ጥቃት ሊያነሳሳ ይችላል?

## በዙሪያው ያለው ሁኔታ

- በንግግሩ ምክኒያት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚደርስበት አካል/ቡድን አለ?
- የግጭት ታሪክ ወይም አድልዎ አለ?

# የጥላቻ ንግግር
# እንዴት እንከላከል?

- በፍጥነት ከማጋራት ይቆጠቡ
- ለማብሰልሰል ጊዜ ይውሰዱ




- ሀላፊነት የሚሰማው የበይነመረብ ተጠቃሚ በመሆን ማህበራዊ ድረ-ገፆች ላይ የሚያገኙትን የጥላቻ ንግግር ባለማጋራትና ሪፖርት በማድረግ ሀላፊነትዎን ይወጡ

# አድራሻ


የመብቶችና ዴሞክራሲ እድገት ማዕከል
ኢሜል፡ info@cardeth.org
P.O.Box፡ 30174
www.cardeth.org
አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ


ሐምሌ, 2012